አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፪ቀን ፪ሺ፲

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 20
Addis Ababa, 21st December, 2017

**<u>ማውጫ</u>**

**<u>ደንብ ቁጥር ፺፮/፪ሺ፲</u>**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሕገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድና የስጋ ዝውውርን ለመቆጣጠር የወጣ ደንብ ገጽ-----------------------------ሺ፫፻፳፩**

**<u>CONTENTS</u>**

**Regulation No 96/2017**
**The Addis Ababa City Government Illegal Animal Slaughter and Meat Trafficking Control Regulation**
**Page-----------------------------------1321**

## <u>ደንብ ቁጥር፺፮/፪ሺ፲ ዓ.ም</u>

## <u>በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሕገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድና የስጋ ዝውውርን ለመቆጣጠር የወጣ ደንብ</u>

የአዲስ አባበ ከተማ ዕድገት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና ከተማዋ ቀድሞ ከነበረችበት ደረጃ በከፍተኛ ፍጥነት እየተለወጠች ትገኛለች፤ የነዋሪው ሕዝብ ቁጥር እንዲሁ በፍጥነት እያደገና በማንኛዉም መልኩ ዘመናዊነትን እየተላበሰ ከተማዋ ለነዋሪዎቿና በተለያዩ ጉዳይ ወደ ከተማዋ የሚመጡትን እንግዶች ጤንነት መጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የእንስሳት ሀብት በሚገባ ጥቅም ላይ ለማዋልና ለማልማት፤ ጤናማ እንስሳትን ለእርድ ማቅረብና የስጋ ምግብ ዉጤቶች በጠቅላላዉ ለሰዉ ምግብነት ተስማሚ መሆኑን ለማረጋገጥ ተመጋቢዎችን ጤንነት ለመጠበቅ እንዲቻልና ጤንነቱ ያልተረጋገጠ እንስሳት እርድንና የስጋ ዝውውርን መግታት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## <u>Regulation No 96/2017</u>

## <u>The Addis Ababa City Government Illegal Animal Slaughter and Meat Trafficking Control Regulation</u>

**WHEREAS**, it is found necessary to cope with rapid change from the pre-existing standard and development of Addis Ababa City; population growth with modernization and to protect the health of society and guests who arrive for different reasons to the city;

**WHEREAS**, it is found necessary to ban unhealthy and not medically ascertained animal slaughtering and meat trafficking; to provide a healthy medically ascertained meat products in human friendly manner to protect the health of consumers and to properly use and develop animal wealth efficiently;

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለዉ የአዲስ አበባከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፩፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫ ንኡስ አንቀጽ (፩) ረ መሰረት ይህንን ደንብ አዉጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጊዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሕገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድንና የስጋ ዝውውርን ለመቆጣጠር የወጣ ደንብ ቁጥር ፺፮/፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ዉስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር፡-

፩. "**ከተማ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. "**የከተማ አስተዳደር**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. "**ቢሮ**" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ነው፤

፬. "**የእርድ እንስሳት**" ማለት ለምግብነት የሚዉሉ እንስሳት ዳልጋ ከብት፣ በሬ፣ ላም፣ መሲና ጊደር፣ ወይፈን፣ ጥጃ፣ በግ፣ ፍየል፣ አሳማና ግመልን ያጠቃልላል፤

፭. "**የስጋ ላይ ማህተም**" ማለት የእንስሳት ዕርድ አገልግሎት እንዲሰጡ በተፈቀደላቸዉ የቄራ ድርጅቶች ዉስጥ የታረደ ከብት ወይም የዕርድ እንስሳት ስጋ ጤነኛነት ወይም ለሰው ምግብነት ተሰማሚ መሆኑ በቢሮ በተመደበ ስጋ መርማሪ ሐኪም አማካኝነት በተመረመረ ስጋ ላይ የሚደረግ የጤንነት ማረጋገጫ ምልክት ነው፤

፮. "**ቄራ**" ማለት በሌላ ሕግ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግስት፣ በማህበራት፣ በግል፣ የተቋቋመ ጤናማ ስጋ፣ የስጋ ዉጤት፣ የታረደ /ካርካስ/ ወይም ተረፈ ስጋ የሚዘጋጅበት፣ የሚታሸግበት፣ ምልክት በቁጥር የሚለጠፍበት ወይም ማህተም የሚደረግበት ለተጠቃሚዎች ለማሰራጨት ባለፈቃድ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ነው፤

**NOW, THEREFORE**, the Cabinet of the Addis Ababa City Government issued this Regulation pursuant to the power vested on it by Article 23 sub-article (1) f of the Revised Charter Proclamation No. 361/2003 (as amended) has issued this Regulation as follows.

## PART ONE
## GENERAL PROVISION

**1. Short title**

This regulation may be sited as "the Addis Ababa City Government Illegal Animal Slaughter and Meat Trafficking Control Regulation No.96/2017"

**2. Definition**

Unless the context requires otherwise, in this regulation:

1. "**City**" means the Addis Ababa city;
2. "**City government**" means the Addis Ababa city government;
3. "**Bureau**" means the Addis Ababa city government trade bureau;
4. "**Slaughterable animal**" means consumable dewlap cattle, ox, cow, heifer, bull, calf, sheep, goat, pig and camel;
5. "**Meat stamp**" means authentication stamp by veterinary doctor appointed by the bureau confirming the healthiness and suitable consumption for human on slaughtered animal and meat products by the Abattoir organizations;
6. "**Abattoirs**" means licensed organization established to distribute by government institutions, associations, privat sector a processed, packed, stamped, numbered healthy meat, meat product, slaughtered Caracas or meat waste;

፯. "**ህገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድ**" ማለት ከቄራ ውጪ የእንስሳት ዕርድ በማካሄድ ለተመጋቢዎች፣ ለምግብ ቤቶች፣ ለግሮሰሪዎች፣ ለሆቴሎች፣ ወይም ለሱፐር ማርኬቶች ለልኳንዳ ቤት፣ ለንግድ ማሰራጨትና መሸጥ ሲሆን ለራስና ቤተሰብ ፍጆታ የሚውለውን ዕርድ አያጠቃልልም፤

፰."**የታረደ ካርካስ**" ማለት ማንኛዉም የታረደ እንስሳ ለሰዉ ምግብነት የሚውል የእንስሳትን ቆዳ፣ ሾኮና፣ የሆድ ዕቃን፣ ጭንቅላትን፣ ደምና ፈርስን ሳይጨምር ያለዉ ስጋ ማለት ነው፤

፱."**ስጋና የስጋ ውጤቶች**" ማለት ከእርድ እንስሳት የሚገኝ ለማንኛውም ሰዉ ለምግብነት የሚዉል የእንስሳት ስጋና መንኛውም ክፍል ወይም ከዚሁ የተዘገጀ ዉጤት ነው፤

፲. "**የስጋ ማጓጓዣ**" ማለት ለስጋ ማጓጓዣነት የተዘገጀ እና ተፈቀደ ከአሉሚንም የተሰራ ነጭ ቀለም የተቀባ ወይም ንጽህናውን የጠበቀ የስጋና ስጋ ዉጤቶች ማጓጓዣ ወይም የሙቀት መጠን መቆጣጠሪያ ተርሞ ኪንግ የተገጠመለት መኪና ማለት ነው፤

፲፩."**ተቆጣጠሪ**" ማለት ይህን ደንብ ለማስፈጸም ሕገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድና የስጋ ዉጤቶች ዝውውር ለመቆጣጠር በቢሮ የሚመደብ ባለሙያ ነው፤

7. “**Illegal slaughter**” means unauthorized slaughtering for consumption of food providers, groceries, hotels, supermarkets or any kind of distribution or sale except for self and home consumption slaughterin

8. “**Slaughtered Caracas**” means any slaughtered animals for food consumption except animal skin, hoof, stomach organ, head, blood and chime and chyel;

9. “**Meat and meat product**” means any animal meat or meat product ofSlaughterable animal produced only for human food consumption;

10. “**Meat carriage**” means a licensed carriage made by aluminum and painted with white color; a neat vehicle made for transportation of meat and meat product or a vehicle accompanied by thermo king to control temperature;

11. “**Supervisor**” means a professional appointed by the bureau to control illegal slaughtering and meat trafficking;

፲፪. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕግ ሰዉነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## ፫. የደንቡ ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በከተማው አስተዳደር ለራስና ለቤተሰብ ፍጆታ ከሚዉል የእንስሳት ዕርድ ውጭ ከስጋና ስጋ ውጤቶች ጋር ሚገናኝ ስራ የሚሰራ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ፬. ዓላማ

ይህ ደንብ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. የህብረተሰቡን ጤና በህገወጥ የእንስሳት እርድ ከሚተላለፉ በሽታዎች ለመከላከል፤

፪. በሕገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድ ምክንያት ሊከሰት የሚችላዉን ፍትሀዊ ያልሆነ የንግድ ዉድድር ለማስቀረት፤

፫. የስጋና ስጋ ውጤቶችን እንዲሁም ተረፈ ምርቶች ያለ አግባብ እንዳይባክን ለመከላከል እና የቆዳና ሌጦ ምርት እንዳይባክን ለመቆጣጠርና ደረጃዉን እንዲጠብቅ ለማስቻል፤

፬. በሕገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድ ምክንያት የሚያስከትለዉን የአከባቢ ብክለትና የጽዳት ጉድለት ለመቆጣጠር፡፡

12. "**Person**" means natural or legal person interested with personality by law.

## 3. Scope of Application

This regulation shall apply on any person in the city involved in transaction of meat and meat products except for self or home consumption of animal slaughtering.

## 4. Objectives

The regulation shall have the objective as follows:

1. protect the society from transmittable diseases caused by illegal animal slaughter;
2. Avoid unfair trade competition caused by illegal animal slaughter;
3. Control wastage and produce quality meat, meat product and surplus product including skin and leather product;
4. Control environmental pollution and lack of hygiene caused by illegal animal slaughtering;

## ክፍል ሁለት

## ህገ-ወጥ የእንስሳ እርድና የስጋ ዝውውር ስለመከልከሉ

**፭. የእንስሳት ዕርድ ስለ ማስኬድ**

በመኖሪያ ቤት ውስጥ ለራስ ወይም ለቤተሰብ ፍጆታ የሚውል ስጋና የስጋ ውጤቶች ለማግኘት ከሚደረግ ዕርድ ውጪ እርድ የሚካሄደው በቄራ ብቻ ነው፡፡

**፮. ሕገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድ ስለመከልከሉ**

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ ላይ ከተገለጸው በስተቀር ማንኛውም ሰው የእንስሳት ዕርድ ማካሄድ አይችልም፡፡

**፯. ስጋና የስጋ ዉጤቶች ስለማጓጓዝ**

ማንኛውም ሰው ካርካስ ወይም ስጋና የስጋ ዉጤቶችን በስጋ ማጓጓዣ መኪና ብቻ ማጓጓዝ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## የቢሮውና የሌሎች ባለድርሻ አካላት ስልጣንና ተግባር

**፰. የቢሮው ስልጣንና ተግባር**

፩. ህገ-ወጥ እንስሳት ዕርድ እና የታረደ ሥጋ ዝውውርን ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፣ ሥራውን በባለቤትነት እና በበላይነት ይመራ፤

፪. ይህን ሥራ ከሚሰሩ ከባለድርሻ ጋር በትሥሥር መሥራት፤

## PART TWO
## PROHIBITION OF ILLEGAL ANIMAL SLAUGHTERING AND MEAT TRAFFICKING

**5. Animal Slaughtering**

Animal slaughtering is allowed onlyinAbattoirs except for self or home consumption animal slaughtering.

**6. Prohibition of Illegal Animal Slaughtering**

Without prejudice to Article 5 of this regulation, animal slaughtering is not allowed.

**7. Trafficking of Meat and Meat Product**

Caracas, meat, and meat product shall be transported by meat carriage.

## PART THREE
## POWER AND FUNCTION OF THE BUREAU AND OTHER STAKEHOLDERS

**8. Power and Duties of the Bureau**

1. Control illegal animal slaughtering and meat trafficking; take measures; superiorly and responsibly lead the work;
2. Work in collaboration with stakeholders that engage in such activity;

፫. ህገ-ወጥ እንስሳት ዕርድ የሚፈፀምባቸውን ቦታዎች በጥናት ይለያል፤

፬. ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽንና ለደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ያሳውቃል፤

፭.በህገ-ወጥ እንስሳት ዕርድ ቁጥጥር ወቅት የተያዘውን የሥጋ ምርት፣ቆዳና ሌጦ ወደ ሚወገድበት ክፍል ወደ አዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት በተገቢው መንገድ እና አግባብ ሥራውን ማስወገድ አለበት፣

፮. በዚህ ደንብ መሠረት ባለድርሻ አካላት ተግባራቸውን እንዲወጡ ያስተባራል አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

፱. <u>የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽ/ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>

፩. በህገ-ወጥ እንስሳት ዕርድ የተገኘን መረጃ ወዲያውኑ ለንግድ ቢሮ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፣

፪. በህገ-ወጥ እንስሳት ዕርድ የተገኘን መረጃ ወዲያውኑ በንግድ ስር ለሚገኘው ለከተማ ግብርና የሥራ ዘርፍ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፣

፫. በህገወጥ የእንስሳት ዕርድ ጥቆማ ሲደርሰው ፈጥኖ በቦታው በመገኘት ዝርዝር ጉዳዩን ለንግድ ቢሮ ያሳውቅልን፡፡ ከንግድ ቢሮ ጋር በመቀናጀት ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣

፬.. በቁጥጥር ሂደት የያዘውን የሥራ ምርት፣ ቆዳና ሌጦ ለንግድ ቢሮ ያስረክባል፡፡

3. Study and identify places that illegal slaughtering is being carried out;
4. Notify issues related to illegal animal slaughtering and meat trafficking to the Addis Ababa police commission and Office of the Code Enforcement Service;
5. Transport or transfer the meat products, skin and hides captured during illegal animal slaughtering control to the Addis Ababa abattoir organization for their safe and proper removal;
6. Coordinate stakeholders to carry out their duties pursuant to this regulation;

## 9. <u>Power and Duties of the Office of the Code Enforcement Service</u>

1. Immediately notify information obtained about illegal animal slaughtering to the trade bureau in writing;
2. Immediately notify the information obtained about illegal animal slaughtering to the urban agriculture department under the trade bureau;
3. Up on having an information about illegal animal slaughtering, appear on site and notify such to the trade bureau in detail; take legal measures in collaboration with the trade bureau;
4. Hand over the meat products, skin and hides which are captured during controlling process to the trade bureau;

፭. ህገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድ ሊከናወንባቸው ይችላል ተብሎ በተለየ ወይም በተጠረጠሩ ቦታዎ ህገ-ወጥ እርድ እንዳይከናወን ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፡፡

፮. ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድ መከላከልና መቆጣጠርን በተመለከተ የሠራቸውን ሥራዎች በጽኁፍ በየ፫ ወሩ ሪፖርት ለንግድ ቢሮ ያቀርባል፡፡

**፲.<u>የምግብ መድሃኒትና የጤና ክብካ አስተዳደር ቁጥጥርና ባለስልጣን ሥልጣንና ተግባር</u>**

፩. በህገ-ወጥ እንስሳት ዕርድ ቁጥጥር ወቅት ያገኘውን መረጃ ወዲያውኑ ለንግድ ቢሮ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፪. ሥጋና የሥጋ ውጤቶችን ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎች ስለ ስጋና ሥጋ ውጤቶች ምርት አያያዝ በተገቢው መንገድ መሆኑን ይከታተላል

፫. በሥጋ ሥጋ ውጤቶች ለሚሠማሩ ነጋዴዎች የጤና ሰርተፊኬት ማውጣት እና ሰርተፊኬቱ በየስድስት ወሩ መታደስ እንዳለበት የማሳወቅ ሥራ መሥራት አለበት፣

፬. ልኳንዳ ቤቶች ሥጋና የሥጋ ውጤቶችን በተገቢው መንገድ መያዛቸውን መከታተል፡፡

5. Carry out proper controlling on identified or suspected places where illegal slaughtering is being carried out so as to prevent the activity;

6. Present a written report once in every three months to the trade bureau on the prevention and controlling of illegal slaughtering activities that it has carried out.

**10. <u>Power and Duties of Food, Medicine and Health Care Administration and Controlling Authority</u>**

1. Immediately notify information obtained about illegal slaughtering during controlling to the trade bureau in writing;

2. Control the proper handling of meat and meat products of seller of the thereof;

3. Create the awareness of those sellers who want to engage in meat and meat products selling business that having a health certificate and renewal of the thereof every six months is mandatory;

4. Follow up the proper handling of meat and meat products by butcheries.

**፲፩.** **<u>የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን ሥልጣን ተግባር</u>**

፩.ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድና የሥጋ ዝውውር ጥቆማ ሲደርሰው ፈጥኖ በቦታው በመገኘት ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡ ድርጊቱን ለንግድ ቢሮ ያሳውቃል የተያዘውን የሥጋ ምርት፣ቆዳና ሌጦ ለንግድ ቢሮ ያስረክባል፡፡

፪.ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድ ይከናወንባቸዋል ተብሎ የተለያየ ወይም የተጠረጠሩ ቦታዎች መረጃ ሲደርሰው ሕገ-ወጥ እርድ እንዳይከናወን ይከላከላል፡፡

፫.ይህ ደንብ የጣሱ ሰዎች አግባብ ባለው ህግ መሠረት እንዲጠየቁ ያደርጋል፣

፬.ይህ ደንብ ለማስፈፀም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**፲፪.** **<u>ቅጣት</u>**

ቢሮው በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፪/፪ሺ፪ የሚወስዳቸዉ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንደተጠበቀ ሆነው ድርጊቱ አግባብ ባለው ሌላ ሕግ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ይህንን ደንብ መተላለፉ እንደሚከተለው ያስቀጣል፡-

፩. የዚህን ደንብ አንቀጽ ፮ የተላለፈ ማንኛም ሰው ከብር ፲፭ሺ እስከ ብር ፳ሺ በሚደርስ ገንዘብ መቀጫ ወይንም ከ፪ ወር እስከ ፫ ወር በሚደርስ የማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል፤

**11. <u>Power and Duties of the Addis Ababa Police Commission</u>**

1. Appear on site immediately and take legal measures up on having an information about illegal animal slaughtering and meat trafficking; notify the activity to the trade bureau; hand over the meat products, skin and hides to the trade bureau;
2. Prevent illegal slaughtering up on having information about identified or suspected places where illegal slaughtering is being carried out;
3. Cause the inquiry of those individuals who violate this regulation pursuant to the relevant laws;
4. Work in cooperation with stakeholders so as to implement this regulation.

## <u>PART FOUR</u>
## <u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

**12. <u>Penalty</u>**

Without prejudice to administrative measures taken by the bureau in accordance with trade registration and license proclamation No.682/2002, unless the offense is punishable by other law, the violation of this regulation is punishable as follows:

1. The violation of Article 6 shall be punishable by fine from 15,000-20,000 birr or punishable by imprisonment from two month up to three month;

፪. የዚህን ደንብ አንቀጽ ፯ የተላለፈ ማንኛም ሰው ከብር ፯ሺ እስከ ብር ፲ሺ በሚደርስ ገንዘብ መቀጫ ወይም ከ፩ ወር እስከ ፫ ወር በሚደርስ የማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል፤

፫. ማንኛውም ሰው የዚህን ደንብ፤ ሌሎች ድንጋጌዎች ወይም ቢሮው የሚያወጣውን መመሪያ ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ከብር ፭ሺ እስከ ብር ፯ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከ፲፭ ቀን እስከ ፫ ወር በሚደርስ የማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል፤

፬. ድርጊቱ ሲደጋገም የገንዘብ ቅጣቱ እጥፍ ያሆናል፤

፭. ተቆጣጣሪው ቅጣቱ እንዲፈጸም የአንድ ጊዜ ማስጠንቀቂያ የሚሰጥ ሲሆን፤ ካልተፈጸመ በወረዳ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

**፲፫. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛዉም ሰው ይህን ደንብ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፲፬. መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

ቢሮው ይህን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፭. ስለተሸሩ እና ተፈጻሚነት ስለማይኖቸው ህጎች**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ የተደነገጉት ጉዳዮች በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፲፮. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከታህሳስ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም.

ድሪባ ኩማ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

2. The violation of Article 7 shall be punishable by fine from 7,000-10,000 birr or punishable by imprisonment from one month up to three month;
3. Any person who violates any provisions of this regulation or directive issued by the bureau for the execution of this regulation shall be punishable by fine from 5,000-7,000 birr or imprisonment from 15 day up to three month;
4. Recidivism shall be punishable twice by fine;
5. The supervisor shall give a notice once for penalty payment, up on frailer the case shall be executed in the Wereda Social court.

**13. Duty to Cooperate**

Any person shall have the duty to cooperate for the implementation of this regulation.

**14. Power to Issue Directive**

The bureau may issue directive for the implementation of this regulation.

**15. Repealed and Inapplicable laws**

Any regulation, directive or practice which is inconsistent with matter covered by this Regulation shall have no effect.

**16. Effective Date**

The regulation shall enter into force as of the 21st December, 2017.

Done at Addis Ababa, this 21st day of December, 2017.

Diriba Kuma

Mayor of the Addis Ababa City Cabinet

17.

ሺ፫፻፹